# ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ፈላጊዎች

*አዲስ ቶልቻ 05/02/13*

በቅርቡ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከ3 ሺህ በላይ ዜጎች በህገወጥ መንገድ ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ ተደርጎ እንደነበር ይታወሳል። እርግጥ የማፈናቀሉ እርምጃ ተቀልብሶ ወደየነበሩበት መንደራቸው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ ጉዳዩን በተመለከተም ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ሚያዚያ 15፣ 2005 ዓ/ም የመንግስትን የ2005 በጀት ዓመት የስምንት ወራት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓረላማው ባቀረቡት ወቅት ከአንድ የምክር ቤት አባል በጉዳዩ ላይ የቀረበ ጥያቄን መነሻ በማድረግ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የዜጎቻችን መፈናቀል እንደተሰማም የተወሰኑ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የፓርቲዎች አመራሮች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አቋም ሲገልፁ ቆይተዋል። የተቃዋሚዎቹ አቋም ላይ ለጉዳዩ የተሳሳተ ትርጉም እንዲሰጥ የሚያደርጉ አንዳንድ ሃሳቦቸ አሉ የሚል እምነት ስላለኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም በጉዳዩ ዙሪያ ያቀረቡትን ማብራሪያ መነሻ በማድረግ አስተያየት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች "ዜጎች በህገ ወጥ መንግድ ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለዋል፣ በዚህም የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈጽሟል" በሚል ድምፃቸውን ማሰማታቸው ተገቢነት ያለው ቢሆንም፣ ነገሮችን አዛብቶ በማቅረብ ተገቢ ያልሆነ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የተሞከረበት ሁኔታ አመዝኖ ታይቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አቋም ለመያዝ ቀዳሚ የሆነው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መኢአድ ነበር። በተደጋጋሚም ለውጭ የመገናኛ ብዙሃን በተለይ ለአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ መግለጫ ሲሰጥ እንደነበረ አስተውለናል፡፡ መግለጫዎቹን ሲሰጥበት የነበረው ቃና የተፈጸመውን የሰብአዊ መብት ጥሰት መንግስትን ለመቃወም የሚያስችል ድንገት ከሰማይ እንደወረደ ሲሳይ የመመልከት ነገር ይታይበት ነበር፡፡ የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ፕሮግራም ጋዜጠኞችም የነጠረ እውነት ከመዘገብ ይልቅ ጉዳዩን ያለወጉ የማራገብ ትዝብት ላይ የሚጥል ሁኔታ አንጸባርቀዋል፡፡ ይህ የተለመደ ቢሆንም፣ ለሕዝብና ለአገርም የሚጠቅም ነገር መስራት የሚቻለው እውነትና እውነትን ብቻ ይዞ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

መኢአድ በጉዳዩ ላይ በተለይ ለአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ፕሮግራም በሰጠው መግለጫ፣ “በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የሚኖሩ የአማራ ተወላጆች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆናቸው ብቻ የዘር ማጥፋት ወንጀል እየተፈፀመባቸው ነው” ብሏል። ይህን የመኢአድ አቋም ከመመልከታችን በፊት የዘር ማጥፋት ወንጀል ምንነት እንመልከት፡፡

የተባበሩት መንግስታት እኤአ በ1948 የዘር ማጥፋትን ወንጀል ለመከላከልና አጥፊዎችን ለመቅጣት ባወጣው ሰነድ በአንቀጽ 2 ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀልን “አንድን ብሄር፣ ዘር ወይም የሃይማኖት ቡድን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመጥፋት፣ በአባላቱ ላይ ግድያ፣ ከባድ የአካል ወይም የስነልቦና ጉዳት ማድረስ፣ ሆን ብሎ በኑሮ ሁኔታቸው ላይ ጫና ማሳደር፣ የቡድኑ አባላት መዋለድ እንዳይችሉ የሚያደርግ እርምጃ መውሰድ እና ሕጻናቶቻቸውን በግዳጅ ወደ ሌላ ቡድን እንዲዛወሩ ማድረግ” ሲል ይተረጉመዋል፡፡

በቤኒሻነጉል ጉምዝ ክልል  በዜጎች ላይ የተፈፀመው የማፈናቀል እርምጃ ከላይ ከተገለጸው የዘር ማጥፋት ወነጀል ምንነት አንጻር ስናየው መኢአድ እነዳለው የዘር ማጥፋት ወንጀል ያለመሆኑን እንረዳለን፡፡ የማፈናቀሉ እርምጃ መነሻ ህገወጥ የሆነ የኢኮኖሚ ጥቅም ነው። ዜጎቹ በተፈናቀሉበት የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል አንዳንድ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ አመራሮች በአካባቢያው የሚገኘውን ሰፊ ሰው ያልሰፈረበተና ያልለማ፣ ባለቤትነቱ የህዝብና የመንግስት የሆነ መሬት ሲቸበችቡ ነበር የቆዩት። በዚህ የመሬት ችርቻሮ በርካታ ከሌላ አካባቢ የመጡ ዜጎች ጭምር መሬት በመግዛትና በመሸጥ ድርጊት ተሳትፎ እንደነበራቸው ተነግሯል።

ይህ ባለበት ሁኔታ፣ የዚህ ወይም የዛኛው ብሄር ተብሎ ሳይለይ በህገወጥ መንገድ ደን መንጥረው የሰፈሩ ሰዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የሚል መመሪያ ይወርዳል። ይህን መመሪያ እንዲያስፈፅሙ የደረሳቸው የተወሰኑ የክልሉ ዞኖችና ወረዳዎች አመራሮች፣ በህገወጥ መንገድ ደን መንጠረው የሰፈሩ ጥቂት ሰዎች ላይ አተኩረው ህጋዊና ተገቢ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ለወደፊቱም የህዝብና የመንግስት ሃብት የሆነውን መሬት እየቸበቸቡ የመኖር ህገወጥ አላማቸውን ለመፈፀም ይረዳቸው ዘንድ ከእነርሱ መሬት ሳይገዙ የሰፈሩ ከሌላ አካባቢ የመጡ ዜጎችን ነጥለው ቤት ንበረታቸውን በትነው አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ አደረጉ።

ጠቅላይ ሚ/ር ኃይለማርያም ደሳለኝ በዚህ ጉዳይ ላይ ለምክር ቤቱ በሰጡት ማብራሪያ “ከዚህ አካባቢ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የተካሄደው የማፈናቀል ስራ በምርመራ

እንደተረጋገጠው የአማራ ብሄር ላይ ብቻ የተካሄደ አይደለም። ሁለተኛ የሚወጣው የኦሮሞ ብሄር ነበር። በዚህ አካባቢ ፀረ ህዝብ አመለካከት ያላቸው አመራሮች በመኖራቸው ምክንያት የተፈጠረ ችግር ነው። ከእነርሱ ጋር ተስማምቶ መሬት ገዝቶ የሚኖር አማራም ሆነ ኦሮሞ አይነካም። ስለዚህ ጉዳዩ አማራ ወይም ኦሮሞ መሆኑ ላይ ሳይሆን የኪራይ ሰብሳቢነት ግንኙነት ነው። ይህን የኪራይ ሰብሳቢነት ግንኙነት በህዝቦች ላይ፣ በየትኛውም ብሄር ላይ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ወይም የማፈናቀል ተግባር ህገወጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሁን ምርመራው ተጠናቆ ወደሚፈለገው ደረጃ እንዲሄድ ይደረጋል ” ብለዋል፡፡

ከመኢአድ በተጨማሪ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲም በዚሁ ጉዳይ ላይ የያዘውን አቋም አሰምቶናል፡፡ አንድነት በመግለጫው “በቤንሻንጉል ጉምዝ ይኖሩ የነበሩ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከክልሉ እንዲወጡ መደረጉ የኢህአዴግ መንግስት የሚከተለው ቋንቋን መሰረት ያደረገ ፌዴራሊዝም ስርዓት ሳቢያ ዜጎች ተቻችለው ተዛምደውና ተዋደው የሚኖሩበትን አውድ ወደ አስፈሪ አደጋ መቀየራቸውን በግላጭ ያሳየ ነው” ብሏል፡፡

በቅድሚያ ቋንቋን መሰረት ያደረገው የፌደራሊስም አወቃቀር በኢሕአዴግ ፖሊሲ የተወሰነ ሳይሆን የኢፌዴሪ ሕግመንግስ ድንጋጌ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ስለዚህ አንድነት በዚህ አቋሙ የተቃወመው ኢሕአዴግን ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በእያንዳንዱ የረቂቅ አንቀጾች ላይ መክሮ ያጸደቀውን ሕገመንግስት ነው፡፡ ይህ የአንድነት አቋም ፓርቲው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አወቃቀርን በተመለከተ እከተለዋለሁ ከሚለው አቋም የመነጨ ነው፡፡ አንድነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አወቃቀር በብሄር፣ ብሄረሰብ አሰፋፈር ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ መልክአምድራዊ ሁኔታን፤ ተራራ፣ ወንዝ ሸለቆ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት የሚል አቋም ነው ያለው፡፡

አሁን ቤኒሻንጉል ጉምዝ አካባቢ የክልሉ ተወላጅ ያልሆኑ ሰዎች መፈናቀላቸው የአቋሜን ትክክለኛነት ያስረዳልኛል በሚል ነው ያቀረበው፡፡ ይህን አንድነት ከቤኒሻንጉል ጉምዝ የተፈናቀሉ ዜጎችን አስታኮ ያንፀባረቀውን አቋሙን ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ እንመልከተው፡፡

ኢትዮጵያ የየራሳቸው ቋንቋና ባህል ያላቸው፣ በተወሰነ መልከአምድራዊ ወሰን ውስጥ የሚኖሩ የበርካታ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አገር ነች፡፡ እነዚህ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በዘውዳዊው ስርአት ኢዴሞክራሲያዊ በሆነ አፋኝና ጨቋኝ አገዛዝ

ሲማቅቁ ኖረዋል። ይህንኑ ስርአት ሲያገለግል የነበረው የወታደራዊ ቡድን አምባገነን መንግስት ወደስልጣን ከወጣ በኋላም ቢሆን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦችን ነጻነትና ዴሞክራሲያዊ እኩልነትና ተሳትፎ ያረጋገጠ አልነበረም። የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በእነዚህ የመንግስት ስርዓቶች ውስጥ ማንነታቸው በህግ ዕውቅና ተነፍጎት ቆይቷል፡፡ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር በቋንቋቸው የመስራት፣ አካባቢያቸውን ለህዝባቸው ጥቅም አመቺ በሆነ አኳኋን የማልማት መብት አልነበረባቸውም፡፡ በአጠቃላይ አስከፊ የብሄራዊ ጭቆና ተጭኖባቸው ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ይህን ብሄራዊ ጭቆና በፀጋ ተቀብለው አሜን ብለው አልኖሩም፡፡ ጭቆናው ከተጫነባቸው ጊዜ ጀምሮ በተለያየ መንገድ ለብሄራዊ መብትና ነፃነታቸው መከበር ታግለዋል፡፡ ከ1960ዎቹ በኋላ ይህ ለብሄራዊ መብትና ነፃነት የሚደረግ ትግል ወደ ተደራጀ የትጥቅ ትግል ተሸጋገረ፡፡ የኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች በብሄራዊ ነፃነት ግንባር ተደራጅተው በየአቅጣጫው ትግላቸውን ቀጠሉ፡፡ ይህ የብሄራዊ ነፃነት ግንባሮች ያካሄዱት ትግል በመጨረሻ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት የህግ ዕውቅና የነፈገውን የወታደራዊው ቡድን አምባገነን የመንግስት ስርዓት ለመገርሰስ በቃ፡፡

የደርግን ስርዓት በትጥቅ ሲታገሉ የነበሩ በብሄር ላይ የተመሰረቱ የነፃነት ግንባሮች ሃያ ገደማ ነበሩ፡፡ የወታደራዊው መንግስት ፕሬዝዳንት የነበሩት ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም የሚመሩት ስርዓት ከመገርሰሱና አገር ለቀው ከመውጣታቸው ከሳምንታት ቀደም ብለው ባደረጉት የመጨረሻ ንግግራቸው፣ “ትግሬው ይወጋናል፣ ኦሮሞው ይወጋናል፣ አማራውም ይወጋናል፡፡ በአጠቃላይ በብሄር ተደራጅተው የትጥቅ ትግል የሚያደርጉት ድርጅቶች 23 ናቸው” ብለው የገለጹትን ለአስረጂነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ይህ በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ላይ ብሄራዊ ጭቆና ጥሎ የነበረው አሃዳዊ የመንግስት ስርዓት የተገረሰሰው በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች ትግል መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ የመጨረሻው አሃዳዊ የመንግስት ስርዓት - የወታደራዊ ደርግ መንግስት በተገረሰሰ ማግስት ለብሄራዊ ነጻነት የትጥቅ ትግል ሲያካሂዱ የነበሩት የነጻነት ግንባሮች የየራሳቸውን ነፃ መንግስት ከመመስረት ይልቅ በምን አይነት ስርዓት አብረው መኖር እንደሚችሉ በአንድ አዳራሽ ታድመው መከሩ፡፡ በዚህ ምክር መገንጠል በራሱ መድረሻ ሳይሆን ብሄራዊ መብትና ነፃነት ወደሚከበርበት ስርዓት የሚወስድ አንድ አማራጭ መንገድ በመሆኑ፣ በአንድ ሉአላዊ ሀገር ስር ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በፌዴራላዊ ስርዓት

አብረው መኖር የተሻለ በመሆኑ ተስማሙ፡፡ የተለያዩ ብሄሮችን፤ ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን የሚወክሉ የነፃነት ግንባሮች በያዙት አቅም መሰረት የኢ.ፌዴሪ ህገመንግስትን ቀረፁ፡፡

የኢ.ፌዴሪ ህገመንግስት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ ለመኖር የተስማሙበት የቃል ኪዳን ሰነድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሉአላዊ የስልጣን ባለቤቶችም ናቸው። በህገመንግስቱ አንቀፅ 8 የሕዝብ ሉአላዊነት በሚለው ርዕስ ስር ንኡስ አንቀፅ አንድ "የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶች ናቸው" ይላል፡፡ በዚህ ህገመንግስት መሰረት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በሚኖሩበት ወሰን ውስጥ ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በቋንቋቸው እየሰሩ፣ እየተማሩ እርስ በርስ ተከባብረው በእኩልነት የሚኖሩበትን ፌዴራላዊ ስርዓት መስርተዋል፡፡

ይህ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በእኩልነትና በመከባበር የሚኖሩበት ስርዓት አንዱ የበላይ ሌላው የበታች፣ አንዱ ብሄራዊ መብትና ነፃነቱ የተከበረለት፣ ሌላው ብሄራዊ ማንነቱ በህግ ዕውቅና የተነፈገበት ሁኔታን በማስቀረቱ፣ አንዱ በሌላው ላይ ጥላቻና መጠራጠር እንዳያድርበት አድርጓል፡፡ በመሆኑም ከጥላቻ የሚመነጭ ግጭትን አስቀርቷል፡፡

አንድነት የሰሞኑን በቤንሻንጉል ጉምዝ የተፈፀመውን የዜጎች መፈናቀል መነሻ በማድረግ ከላይ በተገለፀው ሁኔታ የተመሰረተው በብሄር ላይ የተመሰረተ ፌዴራላዊ ስርዓት "ዜጎች ተቻችለውና ተዋደው የሚኖሩበትን አውድ ወደ አስፈሪ አውድ የቀየረ" ብሎታል፡፡ ይህ የአንድነት አቋም የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታን ታሳቢ አድርጎ ዕውነት ላይ ተመስርቶ የተሰነዘረ ሳይሆን፣ ፓርቲው ያለውን አገሪቱን የብሄር ብሄረሰቦች መብት በህግ እውቅና ወደተነፈገበት ሞቶ የተቀበረ ስርዓት ለመመለስ ካለው ፍላጎት የመነጨ ነው፡፡

እዚህ ላይ አንድነት እንደ አማራጭ የያዘው መልካአምድራዊ ተራራ፣ ወንዝ፣ ሸለቆ. . . መሰረት ያደረገ ፌዴራላዊ አወቃቀር በኢትዮጵያ ላይ ተግባራዊ ቢደረግ የሚኖረውን ገፅታ መመልከቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ አንድነት እንደሚለው የኢትዮጵያ ግዛቶች በተራራ፣ ወንዝና ሸለቆ ተመስርተው ቢከለሉ፣ አንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ ሁለትና ከዛ በላይ የሆነ ቦታ ላይ መከፋፈሉ አይቀሬ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ብሄሮችና ብሄረሰቦች አንድ ላይ ይጨፈለቃሉ፡፡

ይህ ሁኔታ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች፣ በቋንቋቸው የመስራት፣ ቋንቋቸውን በመማሪያ ቋንቋነት የመጠቀም፣ ታሪካቸውንና ባህላቸውን የማጎልበት እድላቸውን ያጠባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ብሄሮችና ብሄረሰቦች በአንድ ላይ ተጨፍልቀው በቋንቋቸው መስራት መማር የማይችሉበት ሁኔታም ይፈጠራል፡፡ ይህም ተገቢ ያልሆነ የእኔ እበልጥ እኔ ፉክክር በመቀስቀስ የግጭት መንስኤ ይሆናል፡፡

በመሆኑም ቀደም ሲል ያካሄዱት የነጻነት ትግል ውስጥ እንዲገቡ የሚያስገድድ ሁኔታን ያስከትላል፡፡ እናም ግጭትና መጠላላትን የሚያነግሰው ብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተው ሕገመንግስታዊ ፌደራላዊ አወቃቀር ሳይሆን አንድነት የያዘው መልክአምድራዊ ሁኔታ ላይ የሚመሰረት የግዛት አከላለል ነው፡፡

የአንድነት አቋም ላይ የሚታየው ትልቁ ግድፈት አገርን እንደ ህዝብ ሳይሆን እንደ ግኡዝ መሬት ከመመልከት የመነጨ ነው፡፡ ለአንድነት ሰው - ሕዝብ ምኑም አይደለም፡፡ ለአንድነት አገር ማለት መሬት ነው፡፡ ይህ የተስፋፊ ፊውዳላዊ መንግስታት አመለካከት ነው። ቀደም ሲል ኢትጵያውያንን ለብሄራዊ ጭቆና የዳረጉት ስርዓቶች ችግር ከዚህ ስለ አገር ካላቸው አመለካከት የመነጨ ነው።

እዚህ ላይ የራሳቸው ማንነት ያላቸውን ብሄሮችና ብሄረሰቦች መብትና ነፃነታቸውን የሚያስከብሩበትን ዕድል መንፈግ፣ ተመልሰን ያለፍንበትን የብሄራዊ ነፃነት ጥያቄ ማስነሳቱ የማይቀር መሆኑ አጽንኦት ተሰጥቶት ሊታወስ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ የቢኒሻንጉል ጉምዝ ተፈናቃዮችን ገዳይ ወዲህ ከዘር ማጥፋት ወንጀል ጋር ወዲህ ደግሞ የፌደራሊዝም ስርአቱ ችግር እንደሆነ በማቅረብ መኢአድና አንድነት ያካሄዱት ቅስቀሳ ተገቢ ያልሆነና የትም የማያደርስ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ማግኘትን ያለመ ነው፡፡